# ይኸን ያውቁ ኖሯልን !

## *በስልክ አነጋግሪኝ በቀጭኑ ሺቦ*
## *ትዝታ እንዲመጣ ደርቦ ደራርቦ !*

በማለት ገጣሚያን ስንኝ የቋጠሩለትና ድምፃዊያን ጥዑመ ዜማ ያዜሙለት የያኔው የቀጭኑ ሺቦ መልእክት ዛሬ በሃገራችን በኢትዮጵያ የሺቦ አልባው ስልክ ባህር ቀዝፎ፣ የብስ ተሻግሮና አየር ሰንጥቆ ሃሎ መባባል የዘወትር ውልና ልምድ ከሆነ ሰነባበትን፡፡

ከአንድ መቶ ዓመት በላይ ያስቆጠረው የኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን ታሪክ በወቅቱ አዲስ የልማት ፓሊሲ እየተመራ እነሆ ሀገራችን ኢትዮጵያን የሁሉም ዓይነት የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ በማድረግ ዝርጋታው ዳርና መሃል አገር ሳይለይ በአራቱም የሀገሪቱ አቅጣጫ እየተስፋፋ ይገኛል፡፡

በዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ ዘመን የኢትዮጳየን የሥልጣኔ በር ያንኳኳው የስልክ አገልግሎት በቅድሚያ የተዘረጋው ከምስራቅ የሀረር ከተማ ወደ ሃገሪቱ መዲና አዲስ አበባ በ1886 ዓ.ም. ነበር፡፡ እንዲያ እንዲያ እያለ አብዛኛውን ዋና ዋና የሀገሪቱን ከተሞች በማዳረስ በአዝጋሚ ሂደት ሲጓዝ ከቆየ በኋላ ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ ግን ከፍተኛ እመርታ በማሳየት የዓይነት፣ የጥራትና የብዛት ለውጥ በአያሌው አስመዝግቧል፣ ኀብረተሰቡም የዚህ ልማት በሰፊው ተቋዳሽ መሆን ጀምሯል፡፡ እስቲ ለግንዛቤ ያህል አገራችን በአሁኑ ወቅት በቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ ያለችበትን ደረጃ በስታትስቲካዊ መረጃ በመደገፍ ጀባ እንበላችሁ፡፡

በገጠር የስልክ አገልግሎት ሰንጀመር እስከ 2000 ዓ.ም. ድረስ በሃገራችን 9,826 የገጠር ቀበሌዎች የስልክ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የመደበኛ ስልክ ማለትም የቤት ስልክ አገልግሎትንም ስንመለከት እስከ ሰኔ 1999 ዓ.ም. ድረስ በመላ ኢትዮጵያ 486,095

የስልክ ደንበኞች ነበሩ። በ1991 ዓ.ም. የተጀመረው የሞባይል ስልክ አገልግሎት ደንበኞችን ብዛት በሚመለከት እስከ ሰኔ 30 1999 ዓ.ም. ድረስ በመላ ሃገሪቱ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ደርሶ ነበር።

ይህ እንግዲህ በቴሌኮሙኒኬሽን ድርጅት የሚሰጠውን ገና ብዙ መስፋፋት የሚጠበቅበትን የኢንተርኔት አገልግሎትንና በየከተማው የተዘረጉትን የሕዝብ ስልክ አገልግሎት /ማለትም በፍራንክና በካርድ/ አይጨምርም። ሌሎች አገልግሎቶች የብሮድባንድ ኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች 28800፣ በወረዳኔት 541 ወረዳዎች፣ በስኩልኔት በሀገሪቱ ካሉት ውስጥ 641 ት/ቤቶች፣ በአግሪኔት በተለያዩ ቦታ የሚገኙ 29 የግብርና ምርምር ተቋሚት ተጠቃሚ ናቸው።

ኢትዮጵያ ምንም እንኳን የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ በአሁኑ ወቅት በአጭር ጊዜ ሃገሪቱን በስልክ መስመር የመሸፈን ቁርጠኛ እቅድ ተይዞ እንቅስቃሴው በመሳለጥ ላይ ያለበት ወቅት ላይ ብትገኝም እኛ በውጭ ሃገር የምንኖረው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሃገራችን በማሳየት ላይ ባለችው የልማት ግሥጋሴ የበኩላችንን ድርሻ በማበርከት አጋርነታችንን የምናሳይበትና ወገናችንንና ራሳችንን የምንጠቅምበት ወቅት አሁን ነው።

ለተሳትፎ! አቶ ፈቃዱ በየነ / አማካሪ/
ስልክ ቁጥር 202 364 6388
fekadu@ethiopianembassy.org
Embassy of Ethiopia
3506 International Dr. NW
Washington DC. 20008